# ምዕራፍ አንድ

# እኛነታችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ስሞች ትጠራላችሁ፣ የእያንዳንዳቸውን ተግባራት ትናገራላችሁ፣ ጥንቃቄም ታደርጋላችሁ፡፡
- ሶስቱን መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች በመዘርዘር ጥቅሞቻቸውን ታስረዳላችሁ፡፡
- አንዳንድ በአካባቢው የሚታወቁ በሽታዎችን በመዘርዘር መከላከያ ዘዴዎቻቸውን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- የአምስቱን የስሜት አካላት ስሞች በመጥቀስ የእያንዳንዳቸውን ተግባራት ስረዳላችሁ፣ በተግባርም ታሳያላችሁ፡፡
- አንዳንድ የብርሃን፣ የድምፅ፣ የቀለም፣ የጣዕምና የሽታ ምንጮችን ቀለል ያሉ ሙከራዎች በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም፡- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትንና በቡድን መስራትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡


## 1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍላችን

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-<br>• ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን ስሞች ትጠራላችሁ::<br>• ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን እየጠቆማችሁ (እየነካችሁ) ታሳያላችሁ::<br>• ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን ተግባራት ትናገራላችሁ:: |

**ቁልፍ ቃላት**

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች
- የሰውነት ክፍሎች ተግባራት

### 1.1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች




ሥዕል 1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

**ስዕል 1.1ን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ተማሪዎች! ስዕሉ የምን ስዕል ይመስላችኋል?
2. ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
3. ልጁ ስንት እጆች አሉት?
4. ልጁ ለመራመድ የሚጠቀምበት የአካል ክፍል የትኛው ነው?

ተማሪዎች! ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ ተረዳችሁ?

ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት፡- ራስ፣ ፀጉር፣ ጆሮ፣ አይን፣ አፍንጫ፣ እጅ፣ ጣት፣ ደረት፣ ሆድ፣ ወገብ፣ ቅልጥም፣ ጉልበት፣ እግርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## መልመጃ 1.1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ከአንገት በላይ ያሉትን ውጫዊ የአካል ክፍሎች ዘርዝሩ፡፡
2. ከአንገት በታች ካሉት ውጫዊ የአካል ክፍሎች ውስጥ የምታውቋቸውን ስም ጥሩ፡፡

### 1.1.2 የውጫዊ ሰውነት ክፍሎች ተግባራት

ተማሪዎች! ስለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራት መዘርዘር ትችላላችሁ?

**የውጫዊ ሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መለየት**

በጫወታ መልክ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ማጥናት

1. አሥር አሥር ተማሪዎች በመሆን ቡድን መሥርታችሁ በየቡድናችሁ የውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት በመዘርዘር ፃፉ፡፡
2. መምህራችሁ ለየቡድኑ ዕድል ሲሰጡ ቡድኑን የሚወክለው አንድ ተማሪ ስለ አንድ ውጫዊ የሰውነት ክፍል ተግባር ሲገልጽ ሌሎቹ የክፍል ተማሪዎች ደግሞ ስለየትኛው የሰውነት ክፍል እንደተገለጸ ይናገራሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ለቡድኖች በየተራ ዕድል እየተሰጠ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት በጫወታ መልክ አጥኑ፡፡




ልጁ ምን እያደረገ ነው?



ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?



ወገብ አጎንብሶ ስራን ለመስራት ይጠቅማል



እግር ለመራመድ ወይም ለመሮጥ ያገለግላል

ሥዕል 1.2 የሰውነት ክፍሎች ተግባራት


## መልመጃ 1.2

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን የአካል ክፍሎች በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተግባራት ጋር በመስመር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እጅ | ለማየት |
| 2. ፀጉር | ለመራመድ |
| 3. አይን | ለማሽተት |
| 4. እግር | ራስን ለመሸፈን |
| 5. አፍንጫ | ዕቃን ለማንሳት |

### 1.1.3 ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚደረግ ጥንቃቄ

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያሉትን ስዕሎች ተመልከቱ።



የህፃኑ እናት ምን እያደረገች ነው?



ስዕሉ ምንን ያሳያል?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?



ከስዕሉ ምን ትረዳላችሁ?



ልጁ ምን እያደረገ ነው?



በሥዕሉ የሚታየው ልጅ ምን እያደረገ ነው?



ስዕሉ ምንን ያሳያል?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?

ሥዕል 1.3 ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚደረግ ጥንቃቄ

ተማሪዎች ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ምን ምን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ተገነዘባችሁ?

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ጤንነት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርብናል::

1. እጅን፣ እግርን፣ ፊትንና፣ ፀጉርን መታጠብ
2. ገላን መታጠብ
3. የአፍንጫንና የጆሮን ፅዳት መጠበቅ
4. ጥፍርን መቁረጥ
5. ፀጉርን ማበጠር

**ተማሪዎች!** ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችንን ማፅዳት ይገባናል:: እስኪ ልጆች ንፅህናን ከመጠበቅ አንፃር የውኃን ጥቅም ተናገሩ::

## መልመጃ 1.3

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ::**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ከአንገት በላይ ያለው የአካል ክፍላችን የቱ ነው?
   ሀ. ሆድ ለ. እግር ሐ. ደረት መ. አይን
2. ራሳችንን ከብርድ ለመከላከል የሚረዳን የቱ ነው?
   ሀ. ቅንድብ ለ. ጆሮ ሐ. ፀጉር መ. ግንባር

**ለ. በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩትን የአካል ክፍሎች በ"ለ" ስር ከተዘረዘረው ጥቅማቸው ጋር በመስመር አዛምዱ::**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንገት | ለመቅመስ |
| 2. ምላስ | ዞሮ ለማየት |
| 3. ጥርስ | ለማኘክ |
| 4. ጆሮ | ለመስማት |

**ሐ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ከምግብ በፊትና ከምግብ በኋላ እጅን መታጠብ አስፈላጊ ነው::
2. የእጅና የእግር ጥፍሮች ቢያድጉም በጤናችን ላይ ጉዳት አያመጡም::
3. እግርን በየቀኑ መታጠብ ያስፈልጋል::

**መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. ፀጉርን መታጠብ ለምን ይጠቅማል?
2. አፍንጫ በምን ይፀዳል?
3. ምግብ ከመመገባችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?

## 1.2 መሠረታዊ ፍላጐቶች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡- <br>• ሶስቱን መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ትዘረዝራላችሁ፡፡ <br>• ስለሶስቱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ጥቅም ታስረዳላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃላት**

- መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች
- መጠለያ
- ምግብ
- ልብስ

### 1.2.1 ሶስቱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች

ተማሪዎች! ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ፡፡



ምግብ ለእድገት ይጠቅማል



ልብስ አካልን ይሸፍናል



ቤት ከዝናብ፣ ከፀሃይና ከአደጋ ይከላከላል

ሥዕል 1.4 የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች

የሰው ልጅ ለመኖር ሶስት መሠረታዊ ነገሮች ሊሟሉለት ይገባል፡፡
ሶስቱ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ተማሪዎች! የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን እንደሆኑ ከሥዕሎቹ ተረዳችሁ?
ሶስቱ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች የምንላቸው፡-

1. ምግብ
2. ልብስና
3. መጠለያ ናቸው፡፡

ከነዚህ መሠረታዊ ፍላጐቶች አንዱ እንኳን ቢጐድል ምን የሚያስከትል ይመስላችኋል? ሐሳባችሁን ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

### 1.2.2 መሠረታዊ ፍላጐቶችና ጠቀሜታቸው

#### ሀ. ምግብ

- ተማሪዎች ስለ ምግብ ምንነት ታውቃላችሁ?
- በጣም የምትወዱት የምግብ ዓይነት ምንድነው?

ተማሪዎች! ከዚህ በታች የቀረቡትን ስዕሎች በደንብ ተመልከቱ፡፡





ሥዕል 1.5 የምግብ ጥቅም ለአካላዊ እንቅስቃሴ

ከስዕሎቹ ምን ተረዳችሁ?

ምግብ:- - ለጤንነት
- ለአካላዊ ዕድገት
- ሙቀትና ጉልበት ለማግኘት ይጠቅማል፡፡

ተማሪዎች! የምግብ መለያ ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

የምግብ መለያ ባህርያት አራት ናቸው፡፡

እነርሱም፡-

1. ጣዕም ------------------- ጣፋጭ፣ ኮምጣጣ
2. ሁነት ------------------- ፈሳሽ፣ ጠጣር
3. ቀለም ------------------ ነጭ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ
4. መአዛ ------------------- ጥሩ ሽታ፣ መጥፎ ሽታ ናቸው፡፡

## ለ. ልብስ

*ተማሪዎች ልብስ ለምን ለምን ይጠቅማል?*

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ፡፡**



- በስዕሉ የሚታየው ልብስ ምንድነው?



- ይህ ምን ዓይነት ልብስ ነው?



- ይህ ልብስ ምን ይባላል?
- ከምን የተሠራ ይመስላችኋል?



- በስዕሉ የሚታየው ልብስ ምንድነው?



- በስዕሉ የምታዩት ልብስ ምንድን ነው?



- ይህ ልብስ ምንድን ነው?
- ምን ጊዜ የሚለበስ ይመስላችኋል?



- የዚህ ልብስ መጠሪያ ስም ምንድን ነው?
- ለምን አገልግሎት የሚውል ይመስላችኋል?

ሥዕል 1.6 የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች

ተማሪዎች! ልብስ ከምን ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል?

ልብስ 1. በተፈጥሮ ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች

ለምሳሌ፡- ሀ. ከጥጥ

ለ. ከቆዳ

ሐ. ከበግ ፀጉር (ከሱፍ) ይሰራል።

2. ከሰው ሠራሽ ጥሬ ዕቃዎች

ለምሳሌ፡- በፋብሪካ ከተመረተ ጨርቅ መሥራት ይቻላል።

## መልመጃ 1.4

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ከቆዳ ምን ምን ዓይነት ልብሶችን መስራት ይቻላል?
2. ከጥጥ ምን ምን ዓይነት ልብሶች እንደሚሰሩ ተናገሩ።
3. ከበግ ፀጉር ምን ምን ዓይነት ልብሶች ይሠራሉ?
4. በስዕል 1.6 ላይ የሚገኙትን ስዕሎች በመመልከት ከምን ከምን እንደሚሰሩ ተናገሩ።

### የልብስ ጥቅም

ተማሪዎች! ልብስ ምን ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ለመምህራችሁ ንገሩ።

ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ስዕሎች በመመልከት የትኞቹ የልብስ ዓይነቶች በየትኞቹ ጊዜያት እንደሚለበሱ ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።



ስዕል 1.7 የልብስ ጥቅም

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የልብስ ጥቅሞች ናቸው፡፡**

- ከብርድ፣ ከፀሐይና ከዝናብ ለመከላከል
- ለውበት ወይም ለጌጥ
- ገላን ለመሸፈን

## መልመጃ 1.5

**ከዚህ በታች በ"ሀ" ሥር የተቀመጡትን የልብስ ጥቅሞች በ"ለ" ሥር ከተቀመጡት የልብስ ዓይነቶች ጋር በመስመር አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ብርድን ለመከላከል የሚለበስ ልብስ | ሀ. ነጭ ሸሚዝ |
| 2. ዝናብን ለመከላከል የሚለበስ ልብስ | ለ. ወፍራም ጋቢ |
| 3. ሙቀትን ለመቀነስ የሚለበስ ልብስ | ሐ. የዝናብ ልብስ |

### ሐ. መጠለያ

**ተማሪዎች! መጠለያ ማለት ምን ማለት ነው?**

በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የመጠለያ ዓይነቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

መጠለያ ማለት ሰዎች ተሰባስበው የሚኖሩበት (የሚጠለሉበት) ቤት ማለት ነው፡፡

### የመጠለያ ጥቅሞች

**ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተመልክታችሁ የመጠለያን ጥቅም ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡**



- በሥዕሉ የምትመለከቱት ቤት ምን ጥቅም እየሰጠ ነው?



- በሥዕሉ የምትመለከቱት የዱር እንስሳ በቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች በቀላሉ ለማጥቃት የሚችል ይመስላችኋል?

ሥዕል 1.8 የመጠለያ ጥቅም

**ተማሪዎች!** በአጠቃላይ መጠለያ:-

1. ከዝናብ
2. ከፀሐይ
3. ከአውሬ (አደጋ ከሚያደርስ የዱር እንስሳ)
4. ከንፋስና ከመሳሰሉት ለመከላከል ይጠቅማል::

**መጠለያዎች:-**

- ከሣር
- ከሲሚንቶ
- ከቆርቆሮ
- ከአሸዋ
- ከሸክላ
- ከብረት
- ከጭቃ
- ከብሎኬት
- ከእንጨት ሊሠሩ ይችላሉ



ሀ. ከቀርከሀ የተገነባ የሣር ክዳን ቤት



ለ. በእንጨትና በጭቃ የተገነባ የቆርቆሮ ክዳን ቤት



ሐ. በሸክላ የተገነባ የቆርቆሮ ቤት



መ. በብሎኬት የተገነባ ፎቅ

ሥዕል 1.9 የቤት ዓይነቶች

## መልመጃ 1.6

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

1. ጋቢና ነጠላ ከጥጥ ይሠራሉ፡፡
2. ቤትን ከእንጨት፣ ከሣርና ከጭቃ መስራት ይቻላል፡፡
3. መጠለያ ከፀሐይና ከዝናብ ይከላከላል፡፡
4. ምግብ በህይወት ለመኖር አስፈላጊ ነው፡፡
5. ምግብ ልብስና መጠለያ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ናቸው፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ በብርድ ጊዜ የሚለበሰው የትኛው ነው?
   ሀ. ሸሚዝ ለ. ጋቢ ሐ. ካናቴራ መ. የናይለን ልብስ
2. ልብስ የሚሠራው
   ሀ. ከጥጥ ለ. ከቆዳ ሐ. ከናይለን መ. ከሁሉም
3. ከሚከተሉት ውስጥ ኮምጣጣ ጣዕም ያለው የቱ ነው?
   ሀ. ሙዝ ለ. ሎሚ ሐ. ፓፓያ መ. ሸንኮራ አገዳ
4. ከሚከተሉት ውስጥ የመጠለያ ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ከአደገኛ ዱር እንስሳት መከላከል ሐ. ከዝናብ መከላከል
   ለ. ገላን መሸፈን መ. መልሱ የለም

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. የመጠለያ ጥቅሞችን ዘርዝሩ፡፡
3. የምትማሩበት ክፍል ከምን የተሠራ ነው?
4. ምግብ ለምን ለምን ይጠቅማል?

## 1.3 ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የታወቁ በሽታዎች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-<br>• ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የታወቁ በሽታዎችን ስም ትጠቅሳላችሁ፡፡<br>• የታወቁ በሽታዎችን ለመከላከል የሚረዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን ትገልፃላችሁ፡፡ |


## ቁልፍ ቃላት

- ህመም
- ተላላፊ በሽታ
- ተላለፊ ያልሆነ በሽታ

ተማሪዎች! የሚከተሉትን ስዕሎች በደንብ ተመልከቱ:: ከስዕሎቹ ምን ተረዳችሁ?



ጤነኛ ልጅ



ታማሚ ልጅ

ሥዕል 1.10 ጤነኛና ታማሚ ልጆች

የተለያዩ በሽታዎች በሰዎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ::

ተማሪዎች! ህመም ምንድን ነው? ጤና ማለትስ ምን ማለት ነው? ከዚህ በፊት ታማችሁ ታውቃላችሁ? በታመማችሁ ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማችሁ ነበር? መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ::

መታመም ማለት የጤንነት መጓደል ማለት ነው:: ህመም ሲኖር ደግሞ በአካልና በአእምሮ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል::

የጤና መጓደል ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ሰውነታችንና አእምሮአችን በትክክል ከሠራ ሙሉ ጤነኞች ነን እንላለን:: ሁላችንም ደስተኛ ኑሮ ለመኖር እንፈልጋለን:: ደስተኛ ኑሮ ለመኖር ደግሞ ጤናችን የተሟላ መሆን አለበት::

ተማሪዎች! ጤንነታችን የተሟላ ከሆነ

- ጨዋታ ለመጫወት
- የፈለግነውን ሥራ ለመሥራት
- በአግባቡ ትምህርታችንን ለመማር እንችላለን::

- ጤነኞች ካልሆንን ምን ዓይነት ችግሮችን የሚያስከትልብን ይመስላችኋል?
- በሽታ ማለት ምን ማለት ነው?

በሽታ የውስጥ ወይም የውጭ አካላችንን በመጉዳት ሰውነታችን የዕለት ተዕለት ተግባሩን በትክክል እንዳያከናውን የሚያደርግ የጤና መታወክ ነው::

በሽታ በሁለት ይከፈላል:: እነርሱም

ሀ. ተላላፊ በሽታና

ለ. ተላላፊ ያልሆነ በሽታ ናቸው::

### ሀ. ተላላፊ በሽታ

ተላላፊ በሽታ ከበሽተኛው ሰው ወደ ጤነኛ ሰው በጥቃቅን ተሃዋስያን አማካኝነት የሚተላለፍ የበሽታ ዓይነት ነው::

**ምሳሌ:-** ጉንፋን፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ ኮሌራና የመሳሰሉት

### ለ. ተላላፊ ያልሆነ በሽታ

ይህ የበሽታ አይነት ደግሞ ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው አይተላለፍም:: በመሆኑም በበሽተኛው አካል ውስጥ በሚፈጠር ችግር የሚከሰት ነው::

**ምሳሌ:-** የስኳር በሽታ፣ የጨጓራ በሽታ፣ የደም ግፊት፣ የደም ማነስና የመሳሰሉት ናቸው::

*ተማሪዎች!* ስለ በሽታ ስትማሩ ብዙ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በሽታዎች እንዳሉ አትዘንጉ::

በዚህ ክፍል ስለ:-

- ጉንፋን
- ወስፋት
- ወባ
- ተቅማጥና
- የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ መንስኤዎችና ስለሚያደርሱት ጉዳት ትማራላችሁ::

## 1. ጉንፋን

የጉንፋን በሽታ የሚከሰተው በቫይረስ አማካኝነት ነው:: ቫይረሶች በጣም ጥቃቅንና በዓይን የማይታዩ ተሃዋስያን ናቸው:: ጉንፋን የሚዛመተው በአየር ውስጥ ነው:: በሽታው ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው የሚተላለፈው በትንፋሽ፣ የመመገቢያ እቃዎችን በጋራ በመጠቀም፣ አፍንጫንና አፍን ሳይሸፍኑ በመሳልና በማስነጠስ ምክንያት ሊሆን ይችላል::



ሀ. ጉንፋን እንዳይተላለፍ የሚደረግ ጥንቃቄ



ለ. በጉንፋን የተያዘ ሰው ጥንቃቄ የጎደለው አሳሳል

ሥዕል 1.11 የጉንፋን መተላለፊያ መንገድና እንዳይተላለፍ ሲደረግ የሚገባው ጥንቃቄ

- ተማሪዎች! የጉንፋን በሽታ ጉንፋን ከያዘው ሰው ወደ ጤነኛ ሰው እንዴት እንደሚተላለፍ ከስዕል 1.11 ተረዳችሁ?
- ጉንፋን የያዘው ሰው ምን ምን ምልክቶች ይታዩበታል? ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።

ጉንፋን የያዘው ሰው የተለያዩ ምልክቶች ይታዩበታል።

- የራስ ምታት
- ማስነጠስ
- አክታ
- የንፍጥ መዝረክረክና የመሳሰሉት ምልክቶች ይታዩበታል።

ተማሪዎች! የጉንፋን በሽታ እንዳይዘን ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን?

የጉንፋን በሽታ የያዘው ሰው ካጋጠመን በሽታው እስከሚሻለው ድረስ

- ወደ ታመመው ሰው አለመቅረብ
- በአንድ የመመገቢያ ዕቃ አብሮ አለመመገብ
- በመኖሪያ ቤታችንም ሆነ በትምህርት ቤት ክፍሎች ውስጥ ተገቢው የአየር ዝውውር እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል።

ጉንፋን ከያዘን ደግሞ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይኖርብናል።

- በቂ እረፍት መውሰድ
- ፍራፍሬዎችን መመገብ
- ትኩስ መጠጦችን መጠጣትና ካልተሻለን ደግሞ ወደ ሐኪም ቤት ሄዶ መታከም
- በሽታው ወደ ሌላ ሰው እንዳይተላለፍ ስንስልና ስናስነጥስ መሀረብ መጠቀም

## 2. ወስፋት

**ተማሪዎች!** ስለ ወስፋት በሽታ ምን ታውቃላችሁ?

የወስፋት በሽታ እንዴት እንደሚመጣ የምታውቁትን ያህል ለመምህራችሁ ንገሩ።



ሀ. የተበከለ ውሃ



ለ. የወስፋት ትል

ሥዕል 1.12 ለተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጥ የተበከለ ውሃ

የወስፋት በሽታ በተለይ ህፃናትን በጣም የሚያጠቃው ለምን ይመስላችኋል? ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።

ህፃናት በወስፋት በሽታ የሚጠቁት በተለያዩ ምክንያቶች ነው። ለምሳሌ፡-

- ባለማስተዋል የተበከለ ውሃ ስለሚጠጡና የተበከለ ምግብ ስለሚመገቡ
- የወስፋት እንቁላል የያዘ አፈር ነክተው እጃቸውን በሳሙና ሳይታጠቡ ስለሚመገቡ ሊሆን ይችላል።

የወስፋት ትል የወስፋት በሽታን የሚያስከትል ጥገኛ ትል ነው። በወስፋት በሽታ የተጠቃ ሰው በሜዳ ላይ ቢፀዳዳ ዓይነ ምድሩ በተለያዩ መንገዶች ወደ ውኃ አካላት ገብቶ ብክለት ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም በሽታው በተበከለ ውኃና ምግብ አማካኝነት ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል።

የወስፋት ትል ወደ ሰውነት ውስጥ ከገባ በኋላ በአንጀት ውስጥ ይራባል። ከዚያም እንቁላሉ ከበሽተኛው አይነምድር /ሰገራ/ ጋር በመውጣት በተለያዩ መንገዶች ወደ ጤነኛ ሰው ይገባል።

የወስፋት በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በወስፋት በሽታ የተያዘ ሰው ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

- የሰውነት መክሳት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ

- የድካም ስሜት
- ማቅለሽለሽና ምራቅ መትፋት

የወስፋት በሽታን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡ የወስፋት በሽታ መከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የምንመገባቸውን ምግቦች መሸፈን
- ቤትና አካባቢን በንጽህና መያዝ
- ውሃን አፍልቶ መጠጣት
- ውሃን አክሞ /ውሃ አጋርን በመጨመር/ መጠቀም
- መፀዳጃ ቤቶችን መጠቀም

## 3. የወባ በሽታ

የወባ በሽታ ፕላዝሞዲየም በሚባል ጥገኛ ህዋስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡ ይህ በሽታ በወባ ትንኝ አማካኝነት ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል፡፡

**ተማሪዎች! የወባ በሽታ ምልክቶችን ታውቃላችሁ? ምን ምን ናቸው?**

በወባ የተያዘ ሰው የሚከተሉት ምልክቶች ይታዩበታል፡፡

- ማንቀጥቀጥ
- ማቅለሽለሽ
- ትኩሳት
- ማላብ
- ከፍተኛ ራስ ምታት
- የምግብ ፍላጎት ማጣት

ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ሲስተዋሉ በአስቸኳይ ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ መታከም አስፈላጊ ነው፡፡


**የወባ በሽታን እንዴት መከላከል እንችላለን? ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡**

የወባ በሽታን ለመከላከል ከሚያስችሉ ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

- የወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑትን የውሃ አካላት ማድረቅ
- በመኖሪያ ክፍል ውስጥ ፍሊት መንፋት
- መኝታን በአጐበር መሸፈን ናቸው፡፡



ስዕሉ ምንን ያሳያል?



ከስዕሉ ምን ትረዳላችሁ?

ሥዕል 1.13 የወባ መከላከያ መንገዶች

የወባ ትንኝ በአካባቢያችሁ ትገኛለች? ማታ ማታ ምን ዓይነት ድምፅ ታሰማለች? ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

## 4. ተቅማጥ

ተማሪዎች! ተቅማጥ በሽታ ይዟችሁ ያውቃል? በሽታው እንዴት የሚከሰት ይመስላችኋል?

የተቅማጥ በሽታ የተበከለ ውሃና ምግብ ስንመገብ የሚመጣ በሽታ ነው። የተቅማጥ በሽታ በምን በምን መንገዶች እንደሚተላለፍ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ። የተቅማጥ በሽታ በተለያዩ መንገዶች ይተላለፋል። እነዚህም:-

- የተበከሉ ቁሳቁሶችን መጠቀም
- በተበከለ እጅ ምግብን መብላት
- የተበከለ ውሃን መጠጣት
- የተበከሉ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን መመገብ ናቸው።

የዚህ በሽታ ምልክቶች ደግሞ፡-

- ራስ ምታት
- ቁርጠት
- ትኩሳት
- ድካም
- የምግብ ፍላጐት መቀነስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ይህ በሽታ በወቅቱ ካልታከሙት እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችል ነው፡፡

### የተቅማጥ በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል?

በሽታውን ለመከላከል የሚያግዙ የተለያዩ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ምግብ ከመመገባችን በፊትና ከተመገብን በኋላ እጃችንን መታጠብ
- ውሃን አፍልተን መጠጣት
- የተበከሉ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን አለመመገብ
- በተገኘው ቦታ አለመፀዳዳት
- ከመፀዳጃ ቤት መልስ እጃችንን መታጠብ
- ምግብ አቅራቢዎች እጃቸውን ሳይታጠቡ የሚሰጡንን ምግብ አለመመገብ

- በመፀዳጃ ቤት መጠቀም የተቅማጥ በሽታን ለመከላከል እንዴት ይጠቅማል? በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡



ሥዕል 1.14 መፀዳጃ ቤት

## 5. ኤድስ

**ተማሪዎች! ኤድስ ምንድን ነው? የመተላለፊያ መንገዶቹን ታውቃላችሁ? ተወያይታችሁ መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡**


የኤድስ በሽታ ኤች አይ ቪ በሚባል ቫይረስ አማካኝነት የሚከሰት ነው፡፡

- ኤድስ የሚገድልና ፈዋሽ መድኃኒት የሌለው በሽታ ነው፡፡
- ኤድስ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡
- በሽታው ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በደም ንክኪ ነው፡፡

ይህም ሊሆን የሚችለው

- አንድን የህክምና መርፌ ለብዙ ሰው በመጠቀም
- በበሽታው የተያዙ ሰዎች የተጠቀሙብትን ስለታምና ሹል ነገሮችን በመጠቀም
- በመድማት ላይ የሚገኙ ሰዎችን ደም በመንካት ነው፡፡

1. ከዚህ በታች የቀረቡትን ስዕሎች ስም ጻፉ፡፡
2. በእነዚህ ቁሳቁሶች አማካኝነት ኤች.አይ.ቪ እንዴት እንደሚተላለፍ በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡




ሥዕል 1.15 ለኤች.አይ.ቪ መተላለፍ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ቁሳቁሶች

የኤድስ በሽታን ለመከላከል ምን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

ዋና ዋናዎቹ የመከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ህክምና ሲወሰድ አዲስ መርፌ መጠቀም
- ሌላ ሰው የተጠቀመበትን ስለታም ነገር አለመጠቀም
- ከማንኛውም የደም ንክኪ መራቅና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## መልመጃ 1.7

ሀ. የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. ጉንፋን መድሃኒት ያልተገኘለት በሽታ ነው፡፡
2. ተቅማጥ በአየር መበከል ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡
3. የወባ በሽታ ዋና ምልክቱ ማንቀጥቀጥና ማላብ ነው፡፡
4. ከመፀዳጃ ቤት ስንወጣ እጃችንን በሳሙናና በውሃ መታጠብ ያስፈልጋል፡፡
5. የወስፋት በሽታ ንጽህናቸው ባልተጠበቀ ምግብና ውሃ አማካኝነት ይከሰታል፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ተላላፊ በሽታ ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ኤድስ
   - ለ. ጉንፋን
   - ሐ. ወባ
   - መ. ከፍተኛ የደም ግፊት
2. የወስፋት በሽታ ምልክት ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ማስነጠስ
   - ለ. ሆድ ቁርጠት
   - ሐ. ማቅለሽለሽ
   - መ. የምግብ ፍላጐት ማጣት
3. በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ የትኛው ነው?
   - ሀ. ወባ
   - ለ. ጉንፋን
   - ሐ. ወስፋት
   - መ. ኤድስ
4. የተቅማጥ በሽታ ምልክት ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ቁርጠት
   - ለ. ድካም
   - ሐ. ሳል
   - መ. የምግብ ፍላጐት መቀነስ
5. ከሚከተሉት ውስጥ በሰው አንጀት ውስጥ የሚራባው የትኛው ነው?
   - ሀ. የወስፋት ትል
   - ለ. የወባ ትንኝ
   - ሐ. ኤች. አይ. ቪ
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

## 1.4 አምስቱ የስሜት አካላት

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| **ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኂላ፡-**<br>• አምስቱን የስሜት አካላት ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡<br>• የስሜት አካላትን ተግባራት ታስረዳላችሁ፡፡<br>• የታወቁ የብርሃን ምንጮችን ትለያላችሁ፡፡<br>• ቢያንስ ሰባት ቀለማትን ትለያላችሁ፡፡<br>• የማየት ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ፡፡<br>• የታወቁ የድምፅ ምንጮችን ትለያላችሁ፡፡<br>• የመስማት ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ፡፡<br>• የተለመዱ ነገሮችን ጣዕሞች ትገልፃላችሁ፡፡<br>• የመቅመስ ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ፡፡<br>• የማሽተት ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ፡፡<br>• ዕቃዎችን (ነገሮችን) በመንካት ሻካራ ወይም ለስላሳ እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ በማለት ትገልፃላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃል**

- የስሜት አካላት

ተማሪዎች! ስንት ዓይነት የስሜት አካላት አሉ? ስማቸውን መጥራት ትችላላችሁ?

የስሜት አካላት አምስት ዓይነቶች ሲሆኑ

እነርሱም:-

1. አፍንጫ
2. ምላስ
3. ጆሮ
4. ዓይንና
5. ቆዳ ናቸው::

ከዚህ በታች የሚገኙትን ስዕሎች በደንብ ተመልከቱ:: የእያንዳንዱን የስሜት አካል ተግባር ስመምህራችሁ ንገሩ::

| | |
|---|---|
|  አፍንጫ |  ምላስ |
|  ጆሮ |  እጅ |
|  ዓይን | |

ስዕል 1.16 የሰው የስሜት አካላት

## 1. አፍንጫ

ተማሪዎች አፍንጫ የተለያዩ ነገሮችን በማሽተት ለመለየት የምንጠቀምበት የስሜት አካል መሆኑን ተረዳችሁ?

አሁን ደግሞ የተለያየ ሽታ ያላቸውን ነገሮች ምሳሌዎች ለመምህራችሁ ንገሩ::

- መልካም መአዛና መጥፎ ሽታ ያላቸው ነገሮች በሽታቸው ይለያሉ::

የሚከተሉትን ስዕሎች በደንብ ተመልክታችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።




- በሥዕሉ የሚታየው ገንዳ ምን ይዟል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?
- ምን ዓይነት ሽታ የሚሰማቸው ይመስላችኋል?



- በሥዕሉ የሚታየው ቤት የምን ቤት ነው?
- ሰውየው ምን እየደረገ ነው?
- ምን ዓይነት ሽታ የሸተተው ይመስላችኋል?






- ልጁ ምን እየደረገ ነው? ምን ዓይነት ሽታ የሚሰማው ይመስላችኋል?

- ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?
- ምን ዓይነት ሽታ የሚሰማት ይመስላችኋል?

ሥዕል 1.17 የተለያዩ ሽታዎች ሲለዩ

**ተማሪዎች!** ከስዕሎቹ ምን ተገነዘባችሁ? ጥሩ ሽታና መጥፎ ሽታ ያላቸውን ነገሮች በአፍንጫችን መለየት እንደምንችል ተረዳችሁ::

**ተማሪዎች!** ሌላው መገንዘብ ያለባችሁ ጉዳይ ደግሞ በሽታ ብቻ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮች መኖራቸውን ነው:: ስለሆነም የምናሸተው ነገር ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ሳናረጋግጥ ማሽተት የለብንም ማለት ነው::

## መልመጃ 1.8

**የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. መፀዳጃ ቤት በንጽሕና ካልተያዘ መጥፎ ሽታ ያመጣል::
2. ሽቶ ጥሩ መዓዛ አለው::
3. አበባ ጥሩ መዓዛ የለውም::

## 2. ምላስ

**ተማሪዎች!** ምላስ ነገሮችን ለመቅመስ የምንጠቀምበት የስሜት አካል ነው:: በመቅመስ የሚለዩ የጣዕም ዓይነቶችን ለመምህራችሁ ንገሩ::

በምላሳችን በመቅመስ የምንለያቸው የጣዕም ዓይነቶች:-

- ጣፋጭ
- መራራ
- ኮምጣጣና
- ጨዋማ ናቸው::

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በደንብ አስተውሉ::**



ሙዝ ምን ዓይነት ጣዕም አለው?



የሎሚ ጣዕም ምን ዓይነት ነው?



ግራዋ ምን ዓይነት ጣዕም አለው?

ሥዕል 1.18 የተለያየ ጣዕም ያላቸው ነገሮች

**ተማሪዎች!** ሙዝ ጣፋጭ ጣዕም እንዳለው፣ ሎሚ ኮምጣጣ መሆኑንና ግራዋ ደግሞ መራራ እንደሆነ ተገንዝባችኋል? የማናውቃቸውን ነገሮች ሁሉ መቅመስ ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? አንድን ነገር በመቅመስ የምንለየው ጉጂ ወይም መርዛማ ስለአለመሆኑ እርግጠኞች ስንሆን ብቻ ነው።

## መልመጃ 1.9

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ንፁህ ውኃ ጣዕም አለው?
2. ሎሚ ምን ዓይነት ጣዕም አለው?
3. የማር ጣዕም ምን ዓይነት ነው?
4. ጉመን ምን ዓይነት ቀለም አለው?
5. የቲማቲም ቀለም ምን አይነት ነው?

**ለ. በ«ሀ» ሥር የሚገኙትን የተለያዩ ጣዕም ያላቸውን ነገሮች በ«ለ» ሥር ከቀረቡት የጣዕም ዓይነቶች ጋር በመስመር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ስኳር | መራራ |
| 2. ሎሚ | ጣፋጭ |
| 3. ግራዋ | ኮምጣጣ |


## 3. ጆሮ

**ተማሪዎች!** ጆሮ ለምን እንደሚጠቅም ለመምህራችሁ ንገሩ። በመስማት የተለያዩ ድምጾችን መለየት እንችላለን።

በአካባቢያችሁ የምን የምን ድምፅ ትሰማላችሁ? ከእናንተ መካከል የአንዳንድ እንስሳትን ድምፅ ሊያሰሙ የሚችሉ ተማሪዎች አሉ? እጅ በማውጣት መምህራችሁ ሲፈቅዱላችሁ በየተራ ሞክሩ።

**የቤት እንስሳትን ድምፃች በመስማት መለየት**

ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ ውስጥ የምትመለከቷቸውን እንስሳት ድምፃቸውን በመለየት በተገቢው ቦታ ፃፉ። (አንድ ምሳሌ ተሰርቶላችኋል)።

| ተ.ቁ | የእንስሳው ስዕል | የሚያሰማው ድምፅ |
|---|---|---|
| 1 |  | ኩኩሉ |
| 2 |  | |
| 3 |  | |
| 4 |  | |
| 5 |  | |
| 6 |  | |

## መልመጃ 1.10

በ"ሀ" ሥር የቀረቡትን የድምፅ ዓይነቶች በ"ለ" ሥር ከቀረቡት የእንስሳት ስም ጋር በመስመር በማገናኘት አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. በአ በአ | ዶሮ |
| 2. ሚያው | ውሻ |
| 3. ኩኩሉ | ላም |
| 4. ውውው | በግ |
| 5. እምቧ | ድመት |

### የዱር እንስሳት ድምፅ

ከዚህ በታች ያሉት የዱር እንስሳት ምን ዓይነት ድምፅ ያሰማሉ? የዱር እንስሳቱን ድምፅ አስመስላችሁ ለመምህራችሁ አሰሙ።



የወፍ ጫጫታ

ወፍ ምን ዓይነት ድምፅ ታሰማለች?



የጅብ ጩኸት

የጅብ ድምፅ ምን ዓይነት ነው?



የአንበሳ ግሳት

አንበሳ ምን ዓይነት ድምፅ ያሰማል?

ስ ዕል 1.19 የተለያዩ ድምፅ የሚያሰሙ የዱር እንስሳት

### የሞተር ድምፅ

ከዚህ በታች በስዕሉ ላይ የተገለፀው እያንዳንዱ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ዓይነት ድምፅ አለው?



መኪና




አውሮፕላን

ስዕል 1.20 የተለያየ ድምፅ የሚያሰሙ የመጓጓዣ ዓይነቶች

## የሙዚቃ መሣሪያ ድምፅ

**ተማሪዎች! የምታውቋቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች የድምፅ ዓይነቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ::**



ክራር ዋሽንት ከበሮ ማሲንቆ በገና

ሥዕል 1.21 ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች



ሳክስፎን



ጊታር

ስዕል 1.22 ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

### መልመጃ 1.11

**በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የድምፅ ዓይነቶች ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ፃፉ::**


1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________

## የሰዎችን ሁኔታ የሚገልፁ የድምፅ ዓይነቶች

ከዚህ በታች በስዕሉ ላይ ከሚታዩት ሰዎች ምን ምን ዓይነት ድምፅ እንደሚወጣ ለመምህራችሁ ለማሰማት ሞክሩ::



ህፃኑ ሲስቅ



መምህሩ ሲመክሩ



የሰዎች ሑኡታ

ሥዕል 1.23 የተለያዩ የድምፅ ዓይነት መገለጫዎች

### 4. ዓይን

ተማሪዎች! ባለፈው ትምህርታችሁ ዓይን በአካባቢያችን የሚገኙትን ነገሮች ለማየት የምንጠቀምበት የአካል ክፍል መሆኑን ተምራችኋል::
ምን ምን ነገሮችን በማየት መለየት እንችላለን? ምሳሌ ስጡ::

የብርሃን ምንጮችን በማየት መለየት እንችላለን:: በአካባቢያችን የተለያዩ የብርሃን ምንጮች ይገኛሉ:: ለምሳሌ:- ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ በመብራት ላይ የሚገኝ አምፑል፣ ሻማ፣ ኩራዝ፣ ፋኖስና ባትሪ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::


የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልክታችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።



- በስዕሉ የሚታየው የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- ከዚህ የብርሃን ምንጭ ብርሃን የሚታየው ምን ጊዜ ነው?



- ስዕሉ የትኛውን የብርሃን ምንጭ ያሳያል?
- ይህ ብርሃን የሚታየው ምን ጊዜ ነው?



- በስዕሉ ላይ የሚታየው የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- የምናበራው ምን ጊዜ ነው?




- በስዕሉ የሚታየው ሰው የያዘው የብርሃን ምንጭ ምን ይባላል?
- በብርሃን ምንጭነት የምንጠቀምበት ምን ጊዜ ነው?



- በስዕሉ ላይ የሚታዩት ሰዎች ምን እያደረጉ ይመስላችኋል?
- በስዕሉ የሚታየው የብርሃን ምንጭስ ምንድን ነው?
- ይህ የብርሃን ምንጭ ለምን ለምን እንደሚያገለግል ግለጹ::



- በስዕሉ በጐጆ ቤቱ ውስጥ የሚታየው የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- አገልግሎት የሚሰጠው ምን ጊዜ ነው?



- በስዕሉ ላይ የምታዩት የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- በብርሃን ምንጭነት የሚያገለግለው ምን ጊዜ ነው?

ሥዕል 1.24 የተለያዩ የብርሃን ምንጮች

ተማሪዎች! የብርሃን ምንጮች በስንት እንደሚመደቡ ታውቃላችሁ?

የብርሃን ምንጮች በሁለት ይመደባሉ:: እነርሱም

- በተፈጥሮ የሚገኙ የብርሃን ምንጮችና
- ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮች ናቸው::

በስዕል 1.24 ከቀረቡት የብርሃን ምንጮች ውስጥ የትኞቹ ተፈጥሯዊ የትኞቹ ደግሞ ሰው ሰራሽ እንደሆኑ ለመምህራችሁ ግለጹ::

## መልመጃ 1.12

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. በቀን ብርሃንን የምናገኘው ከምንድን ነው?

   ሀ. ከጨረቃ　　ለ. ከፀሐይ　　ሐ. ከኩራዝ

2. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ብርሃን ሰጭ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ፋኖስ　　ለ. ሻማ　　ሐ. ጨረቃ

3. የተለያዩ ነገሮችን ለማየት የሚጠቀመን የአካላችን ክፍል የትኛው ነው?

   ሀ. ዓይን　　ለ. አፍንጫ　　ሐ. ጆሮ

### 5. ቆዳ

ተማሪዎች! የነገሮችን ሻካራነትና ልስላሴ እንዴት እንለያለን?

ቆዳ ውስጣዊ አካላችንን የሚሸፍን የሰውነት ክፍል ነው። የተለያዩ ነገሮችን ሻካራነትና ልስላሴ በጣቶቻችን በመዳሰስ መለየት እንችላለን።

ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮች በእጆቻችን አማካኝነት ሊለዩ ይችላሉ።

- የጣት ቆዳችንን ለመዳሰስ እንጠቀማለን።

ተማሪዎች! የለስላሳና የሻካራ ነገሮችን ምሳሌዎች መስጠት ትችላላችሁ?

**ለስላሳ ነገሮች የሚባሉት፡-** ጥጥ፣ ወረቀት፣ ላስቲክ

**ሻካራ ነገሮች፡-** እንጨት፣ አሸዋ፣ አፈር

ተማሪዎች! የራሳችሁን ልብስ ነክታችሁ ሻካራነቱንና ልስላሴውን በመለየት ለመምህራችሁ ተናገሩ።



ጂንስ ሱሪ ሸካራ ነው



ሸሚዝ ለስላሳ ነው



ቆዳ ጃኬት ለስላሳ ነው



የክር ሹራብ ሸካራ ነው

ሥዕል 1.25 በመዳሰስ ሊለዩ የሚችሉ የልብስ ዓይነቶች



- በስዕሉ የሚታየው ልጅ ዓይኑ እንደተሸፈነ በእጆቹ በመዳሰስ ብቻ የያዘው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚችል ይመስላችኋል?

ስዕል 1.26 ልጁ ዓይኑ እንደተሸፈነ በጠረጴዛ ላይ የተቀመጠለትን ነገር ሲዳሰስ

## መልመጃ 1.13

**ሀ. የሚከተሉትን ነገሮች "ለስላሳ" ወይም "ሻካራ" በማለት ለይታችሁ ጻፉ::**

1. ወረቀት ________________
2. ወለል ________________
3. ጫማ ________________
4. መስታዎት________________
5. አሸዋ ________________
6. ጥጥ ________________
7. አፈር ________________

**ለ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ብርሃን ነገሮችን ለማየት አስፈላጊ ነው::
2. ግራዋ ጣፋጭ ጣዕም አለው::
3. ውሃንና አምቦ ውሃን በጣዕማቸው መለየት ይቻላል::
4. ማር ኮምጣጣ ነው::

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ::**

1. ስኳርና ጨውን በምን እንለያለን?
   ሀ. በቀለማቸው ለ. በሽታቸው ሐ. በጣዕማቸው
2. ለማሽተት የምንጠቀምበት የስሜት አካል የትኛው ነው?
   ሀ. ዓይን ለ. አፍንጫ ሐ. ጆሮ
3. ከሚከተሉት ውስጥ የላምን ድምፅ የሚወክለው የትኛው ነው?
   ሀ. ዉዉዉ ለ. እምቧ እምቧ ሐ. ባአ ባአ
4. የስልክ መልዕክት የምንቀበለው በየትኛው የስሜት አካል ነው?
   ሀ. በዓይን ለ. በአፍንጫ ሐ. በጆሮ

# ማጠቃለያ

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት ራስ፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ እጅ፣ ጣት፣ አንገት፣ ደረት፣ ትከሻ፣ ሆድ፣ ወገብ፣ ቅልጥም፣ ጉልበትና እግር ናቸው።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች እንደ የቅርጻቸውና እንደ አቀማመጣቸው ተግባራቸውም ይለያያል።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ንፅህናቸው መጠበቅ አለበት።
- የሰው ልጅ ሶስቱ መሠረታዊ ፍላጎቶች ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው።
- ምግብ ለሰው ልጆች አካላዊ ዕድገት፣ ጥንካሬና ጉልበት በጣም ጠቃሚ ነው።
- አልባሳት ከፀሐይ ብርሃን፣ ከቅዝቃዜ፣ ከብርድ፣ ከዝናብና ከመሳሰሉት ለመከላከል እንዲሁም ገላን ለመሸፈንና ለውበት ይጠቅማሉ።
- አልባሳት ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከቆዳና ከናይለን ሊሠሩ ይችላሉ።
- መጠለያ ከዝቅቃዜ፣ ከፀሐይ ብርሃን፣ ከዝናብ፣ ከነፋስና ከአደገኛ የዱር እንስሳት ለመከላከል ይጠቅማል።
- መጠለያዎች ከሣር፣ ከእንጨት፣ ከጠፍጣፋ ብረት፣ ከሸክላ፣ ከጭቃ፣ ከሲሚንቶና ከአሸዋ ሊሠሩ ይችላሉ።
- በህፃናት ላይ ከሚከሰቱ በሽታዎች ውስጥ በዋናነት የሚታወቁት ጉንፋን፣ ወስፋት፣ ወባና ተቅማጥ ናቸው።
- ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ በደም አማካኝነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። ስለሆነም ከማንኛውም የሰው ደም ንክኪና በደም ከተበከሉ ሹል ነገሮች መራቅ ያስፈልጋል።
- ኤድስ የሚገድልና መድኃኒት የሌለው በሽታ ነው።
- ጉንፋን በአየር አማካኝነት የሚተላለፍ በሽታ ነው።
- የወስፋት በሽታ በሰው እዳሪ አማካኝነት ይዛመታል። ይኸውም በተበከለ ውሃና በተበከለ ምግብ ወደ ጤነኛ ሰው በመግባት በአንጀት ውስጥ ይራባል።
- የወባ በሽታ ፕላዝሞዲየም በሚባል ጥገኛ ህዋስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው። በሽታው በወባ ትንኝ አማካኝነት ከበሽተኛ ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል።
- የተቅማጥ በሽታ በአሜባና በባክቴሪያ አማካኝነት ይከሰታል።
- ዓይን፣ ጆሮ፣ ምላስ፣ አፍንጫ፣ ቆዳ አምስቱ የስሜት አካላት ናቸው።
- ዓይናችን የተለያዩ ነገሮችን በማየት የምንለይበት የስሜት አካል ነው።
- ማንኛውንም ነገር ለማየት ብርሃን አስፈላጊ ነው። የብርሃን ምንጮች፡- ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ሻማ፣ ባትሪ፣ ኩራዝ፣ የኤሌክትሪክ ብርሃን ወዘተ... ናቸው።

- ዓይናችን የተለያዩ ቀለማትን ለመለየት ይጠቅማል፡፡
- ጆሮ ለመስማት የምንገለገልበት የስሜት አካላችን ነው፡፡
- በጆሮአችን የተለያዩ ድምፆችን እንሰማለን፡፡ የሰማናቸውን ድምፆችም የምን የምን ነገሮች እንደሆኑ መለየት እንችላለን፡፡
- ምላስ የተለያዩ ነገሮችን ለመቅመስ የምንገለገልበት የስሜት አካላችን ነው፡፡
- በምላሳችን ጣፋጭ፣ መራራ፣ ኮምጣጣና ጨዋማ ጣዕሞችን እንለያለን፡፡
- በአፍንጫችን ጥሩና መጥፎ ሽታ ያላቸውን ነገሮች እንለያለን፡፡
- ቆዳ ለመዳሰስ የምንጠቀምበት የስሜት አካላችን ነው፡፡ በእጃችን ቆዳ አማካኝነት ሻካራና ለስላሳ ነገሮችን እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮችን እንለያለን፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. ጽጌረዳ ጥሩ ሽታ አለው፡፡
2. ቀለማትን በመዳሰስ መለየት እንችላለን፡፡
3. ሳቅ የደስታ መግለጫ ነው፡፡
4. የሙዚቃ መሣሪያዎች ሁሉ አንድ ዓይነት ድምፅ አላቸው፡፡
5. ከምላስ በስተቀር ሁሉም የስሜት አካላት ውጫዊ ናቸው፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ብርሃን አመንጭ ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ሻማ ለ. ኩራዝ ሐ. መስታዎት
2. ከሚከተሉት ውስጥ በአየር አማካኝነት የሚተላለፈው በሽታ የትኛው ነው?
   ሀ. ጉንፋን ለ. ተቅማጥ ሐ. ወስፋት
3. ቴሌቪዥን ስንከታተል የትኞቹን የስሜት አካላት እንጠቀማለን?
   ሀ. ዓይንና አፍንጫ ለ. ጆሮና ቆዳ ሐ. ዓይንና ጆሮ
4. መሠረታዊ ፍላጐት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ቤት ለ. መኪና ሐ. ልብስ
5. ጣዕሞችን በምን እንለያለን?
   ሀ. በዓይናችን ለ. በምላሳችን ሐ. በእጃችን

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ስንት ዓይነት ቀለም አለው?
2. የስሜት አካላት የሚባሉት እነማን ናቸው?
3. ሶስት የሰዎችን ስሜት የሚገልጹ የድምፅ ዓይነቶች የሚፈጠሩባቸውን ሁኔታዎች ጻፉ፡፡
4. የሰው መሠረታዊ ፍላጐቶች ስንት ናቸው? ስማቸውን ጻፉ፡፡
5. የተለያዩ ቀለማትን በምን እንለያለን?

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ፡፡*

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቼን ስሞች እጠቅሳለሁ፡፡ ☐
2. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቼን በመንካት አሳያለሁ፡፡ ☐
3. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቼን ተግባራት እናገራለሁ፡፡ ☐
4. ሦስቱን መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች እዘረዝራለሁ፡፡ ☐
5. ስለሦስቱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ጥቅሞች አስረዳለሁ፡፡ ☐
6. ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉትን የታወቁ በሽታዎችን ስሞች እጠቅሳለሁ፡፡ ☐
7. የታወቁ በሽታዎችን ለማስወገድ የሚረዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን እገልጻለሁ፡፡ ☐
8. አምስቱን የስሜት አካላት ስሞች እጠቅሳለሁ፡፡ ☐
9. የስሜት አካላትን ተግባራት አስረዳለሁ፡፡ ☐
10. የታወቁ የብርሃን ምንጮችን እለያለሁ፡፡ ☐
11. ሰባቱን የቀለም ዓይነቶች እለያለሁ፡፡ ☐
12. የማየት ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐
13. የታወቁ የድምፅ ምንጮችን እለያለሁ፡፡ ☐
14. የመስማት ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐
15. የተለመዱ ነገሮችን ጣዕሞች እገልፃለሁ፡፡ ☐
16. የመቅመስ ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐
17. የማሽተት ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐
18. ዕቃዎችን (ነገሮችን) በመንካት ሻካራ ወይም ለስላሳ እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ በማለት እለያለሁ፡፡ ☐